# የአመራር አምላኪዎች ወግ ሲከሽፍ

ዮናስ 03-28-18

የኢህአዴግ ምክር ቤት ስራ አስፈጻሚው ረጅም ጊዜ በመውሰድ በዝርዝር የተመለከታቸው ሃገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች በየብሄራዊ ድርጅቶቹ እንዴትና በምን አግባብ ተፈፃሚ እንደሆኑ መገምገም ከጀመረ ሳምንት አስቆጥሯል፡፡ በዚህ ሂደት ለውጥ መጀመር በራሱ ጥሩ እርምጃ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም ለውጥን ማስቀጠል ትልቅ ፈተና መሆኑን ስለመገንዘቡም አመልክቷል። . . . ወጣቱ የሚፈልገው ወፍራም ማብራሪያ ሳይሆን ተጨባጭ ምላሽ መሆኑን አረጋግጫለሁ ብሏል። የአመራር ክፍተቱን መሙላትም አንዱ አጀንዳ እንጂ አቢይ ጉዳይ አለመሆኑንም እንደዛው።

የተሳተው ነገር ኢህአዴግ አመራር አምላኪ ድርጅት ያለመሆኑ ጉዳይ የሩብ ክፍለ ዘመን እውነታ ነው። በድርጅቱ ሰነድ ላይ በተመለከተው አግባብ አመራሩ ለእርምት ባለው ዝግጁነት ለበለጠ ተጠያቂነት እና ለበለጠ ኃላፊነት ስምሪት የሚሰጥ ድርጅት እንጂ ሹመትን ግቡ ያደረገ መርህ ተከትሎ አያውቅም፤ ወደፊትም በለመደው መርህ ይቀጥላል። ሹመት ሳይሆን ህዝቡ ውስጥ ያለውን ብርቱ የለውጥ ፍላጎት እና ጠንካራ የለውጥ አቅም በሚገባ አስተባብሮ ለመጠቀም ዳር እስከ ዳር መንቀሳቀስ እንደሚጠይቀው የተገነዘበ ለመሆኑም ብቅ እያለ ከሚሰጣቸው መግለጫዎች መገንዘብ ይቻላል።

አመራር አምላኪ የሆኑ ሃይሎች የግምገማውን ቆይታ መነሻ በማድረግ የአመራር ምደባን የተመለከተ ህኩቻ እንዳለ ቢያስወሩም ድርጅቱ በችግር ውስጥ ተሰብስቦ ችግርን እየሞቁ

መሰንበት ዘመኑ የማይፈቅድ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ሙግት ውስጥ የሚገኝ ለመሆኑም መግለጫዎቹ ፍንጭ ይሰጣሉ። ቀደም ብሎ የየብሄራዊ ድርጅቶቹ ማእከላዊ ኮሚቴዎች ባደረጉት ግምገማ በሃገርና በክልል ጉዳይ የተለያየ ሃሳብ ቢኖራቸውም በጋራ ለመስራት የሚከለክላቸው አንዳች ነገር እንደሌለ "ሁላችንንም አንድ የሚያደርገን አጀንዳ የበለፀገ ሃገር እና ክልል መገንባት ነው!" ሲሉ ማስቀመጣቸውም ስለዚህና ድርጅቱ አመራር አምላኪ ባልሆኑ ሃይሎች የተገነባ ግንባር መሆኑን የሚያጠይቅ ነው። "በእጃችን ያለውን ስኬት አሳንሰን ልናይ አይገባም፤ ሃገራችንም ክልላችንም በለውጥ ጉዞ ላይ ናቸው፤ ቁምነገሩ ይህንን ሰፊ ለውጥ የሚመጥን አመራር መስጠትና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በባለቤትነትነት መንፈስ ማሰማራት ነው!" ማለቱም ግንባሩ አመራር አምላኪ በሆኑ ግለሰቦችና ቡድኖች አለመጠለፉን የሚያረጋግጥ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የገዥው ፓርቲ የኢህአዴግ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከመጋቢት ሁለት እስከ መጋቢት አስር ድረስ ሲያካሂድ የቆየውን ስብሰባ ማጠናቀቁን ተከትሎ የፓርቲው ምክር ቤት ስብሰባውን ጀምሮ አጠናቋል። ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባውን ሲያጠናቅቅ በሰጠው መግለጫ በሃገሪቱ ውስጥ እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮችን "የአመራር ድክመት የወለዳቸው" ሲል የገለፃቸው ሲሆን ይህንን ለማረም የሚያስችል "አመለካከት እና አንድነት" የሚፈጥር ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጡንም ተናግሯል። ምክር ቤቱ በጉባኤው ከአንድ ወር በፊት የስልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ያቀረቡትን አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ተክቶ ፓርቲውን በሊቀ-መንበርነት፤ ኢትዮጵያን ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚያስተዳድሩትን መሪ ይመርጣል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረ ሲሆን፤ የትላንትና ማታው የኢ.ቢ.ሲ/ኢ.ቲቪ (ከምሽቱ 4:00) ሰበር ዜና እንዳበሰረው፤ ዶክተር አቢይ አህመድን መርጧል። ይህ ግን ችግሮቹ ሁሉ በአዲሱ ሊቀመንበር ብቻ ይፈታሉ ማለት ሳይሆን ግንባሩ በሚሰጠው የስራ ስምሪት ስለመሆኑ ከላይ የተመለከቱት የግንባሩ መርሆዎች እና የአባል ድርጅቶቹ አቋሞች ቢያጠይቁም፤ አመራር አምላኪ ሃይሎች የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የቤት ስራዎች ምን ምን ናቸው? የሚል ወግ ማውጋታቸውን ቀጥለዋል። ጥቂቶቹን እና በተለያዩ ድረ

ገጾች ያየኋቸውን እነሆ፡-

የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀ መንበር አቶ የሽዋስ አሰፋ  ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ችግሮች ሊቀረፉ የሚችሉት ሕዝቡ በፍላጎቱ በመረጠው ፓርቲ ሲተዳደር መሆኑን ለቢቢሲ የአማርኛው ክፍል የተናገሩ ሲሆን፤ ፓርቲያቸው በህዝብ ምርጫ አብልጦ እንደሚያምን ገልጸው፤ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን የተለየ ፖለቲካዊ አቋም ካላቸው ወገኖች ጋር ለውይይት መቀመጥን ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራና ተቋማዊ ማሻሻዎችን ለማድረግ የሚተጋ መሪ ቢመረጥ ለሃገሪቱ የሚበጅ ነው ይላሉ። ከተመራጩ ጠቅላይ ሚኒስትር ማንነት በበለጠ ይዟቸው የሚመጣቸው ኃሳቦች እንደሚያሳስቧቸው የሚናገሩት አቶ የሽዋ ተስፋቸው የተቀጠበ መሆኑም ነገሩኝ ሲል ቢቢሲ አመልክቷል።

"ኢህአዴግ ከዚህ በፊት በሚጠቅምባቸው ዘዴዎችም ሆነ ማስፈራሪያዎች ሊገዛ አይችልም። ማንም ቢሆን የሚመጣው ማንነቱ ሳይሆን የሚያጓጓን ይዞ የሚመጣው ነገር ምንድነው? ምን ያህልስ የህዝቡንድ ድምፅ ለመስማት ዝግጁ ነው። ይህ ነው እንጂ ኢህአዴግ አንድ ድርጅት አንድ ሥርዓት ስለሆነ በጉጉት የምንጠብቀው የተለየ ነገር   የለንም።" "አዲስ ተሿሚው ጠቅላይ ሚኒስትር ተደቅነው የሚጠብቁት ውስብስብ ፈተናዎችን ለመጋፈጥ ብሎም ለመቅረፍ የፖለቲካ ዝግጁነት፣ ቁርጠኝነት እና አቅም እንዳለው ከወዲሁ ማሳየት ይገባዋል" የሚሉት ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ የፖለቲካ እና የደህንነት ጉዳዮችን የሚያጠኑት ተመራማሪው አቶ ሃሌሉያ ሉሌ ናቸው። ........ አቶ ሃሌሉያ ሉሌ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በሕዝቡ ዘንድ ለተነሱ ጥያቄዎች ዕውቅና ከመስጠት ባሻገር፤ ምላሽ የሚቀርብበት ግልፅ የጊዜ ሰሌዳ ማስቀመጥ እንደሚጠበቅበት፤ ይህም በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት እንደሚጠቅመው ጨምረው መናገራቸውም በዘገባው ተመልክቷል። ሌሎቹም ተመሳሳይ የሆኑና በግለሰብ ላይ የተንጠለጠሉ፤ ይልቁንም የአመራር አምላኪነት ጥግጋትን የሚያጠይቁ ወሳኞችን ለዜና አውታሩ አውግተዋል።

ኢህአዴግ እያወጋ የሚገኘው ደግሞ የዚህን ተቃራኒ እና ከላይ በተመለከተው አግባብ የችግሩን ደረጃና ድርጅታዊ መርሆ ታሳቢ ያደረገ ነው። በኢህአዴግ ባህል የተለያዩ የሹመት ቦታዎች የስራ ስምሪትና ተልእኮ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ በኢህአዴግ ውስጥ ለዘመናት የዘለቀ አብዮታዊ አተያይ እና ተራማጅ ባህል ነው:: በመሰረቱ በኢህአዴግ ለስልጣን ያለው ትክክለኛው አተያይ፤ ስልጣን የህብረተሰቡን ለውጥ ለማፋጠን የሚጠቅም መሳርያ ብቻ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ስልጣን ትልቅ ህዝባዊ ሃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህም ስልጣን የመስዋእትነት ቦታ እንጂ ልክ እንደደርግና መሰሎቹ ሌላ ገዥ መደብ የሚኮንበት መሿጋገርያ ድልድይ አይደለም፡፡ ለዚህ ማጠየቂያው ደግሞ ኢህአዴግ በጥልቅ ተሃድሶው ሂደት ለስልጣን ያለ አተያይ ችግር አለበኝ ብሎ ማመኑና ይቅርታ መጠየቁ ነው፡፡

ሰዎች የስልጣን ቦታን ለሃብት እና ምቾት ካለው ቀረቤታ፤ ለፈላጭ ቆራጭነት ካለው ትስስር እና ከብሄር፣ ከዘር ወይም ከቅርርብ ማየት ሲጀምር ለስልጣን ያለው አተያይ የተበለሸና በአብዛኛው “ድርጅት” የሚለው አላማና ተልእኮ አፈር ድሜ ይበላና የግል ኑሮ ማደላደያ በማድረግ በተዛባና በተሳሳተ መንገድ ይጠቀመዋል፡፡ ሰዎች ለስልጣን ያላቸው አተያይ ትክክለኛ ሲሆን በህብረተሰቡ ውስጥ አስፈላጊውንና ወሳኙን ለውጥ ለማረጋገጥ አስፈላጊውን መስዋእትነት ይከፍላሉ፡፡

አሁን የተለያዩና ከላይ በተመለከተው አግባብ የሚገለጹ አመራር አምላኪ/ስልጣን ፈላጊ ሃይሎች፤ የጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም መልቀቅያ መጠየቅን ተከትሎ ጠቅላይ ሚስትር በመሾምና በማውረድ ላይ ተጠምደው መክረማቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ተግባርም አጠቃላይ ለስልጣን ካላቸው የተዛባ አተያይ የሚመነጫ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በኢህአዴግ ቤት ውስጥ ካለው ዲሞክራሲያዊ ባህል እና ድርጅታዊ አመለካከት ጋር ሲተያይ ፈፅሞ ከመሰረታዊው ሃቅ የራቀ ነው፡፡

በኢህአዴግ ቤት የትኛውም ድርጅታዊ ምደባ የሚታየው ከሚፈለገው ለውጥ እና አጠቃላይ

ተልእኮውን መነሻ በማድረግ ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከቱት አስረጂዎች ባሻገርም መዘርዘር ይቻላል፡፡ የወቅቱን ሁኔታ በጥልቀት እና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመገምገም ለዚህ ለውጥ ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሙግት እንጂ አመራር ላይ የተንጠለጠለ አጀንዳ ምክር ቤቱ የሌለው መሆኑንም በተደጋጋሚ ገልጿል፡፡ በመሰረቱ ይህችን ሃገር ወደ ህዳሴ ጉዞ በመማራት ሂደት መሪዎች የራሳቸው አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም መስመርና ድርጅት ግን ተኪ የሌላቸው ናቸው፡፡ ከግለሰብ በላይ መስመር፤ ከግለሰብ በላይ አላማና ድርጅት ትልቁን ቦታ ይወስዳሉ፡፡ በዚህ ሂደት መላው መዋቅር የለውጡ አካል እንጂ የዚህች ሃገር ህልውና በጠቅላይ ሚኒስትር ቦታና ማንነት ላይ የተንጠለጠለ እጣ ፈንታ የለውም! ሰዎች ይተካካሉ መስመሩ ግን ለመጪ ትውልዶች ጭምር ቀጣይ እና ህያው ሆኖ ይዘልቃል! በሚል መርህ ለለውጥ የሚያበቃቸውን ስንቅ እየሰነቁ መሆኑን የተመለከቱት የግንባሩ መረጃዎች የሚያጠይቁት፤ በኢህአዴግ ቤት ሰው ለስራ እንጂ ቦታ ለሰው የማይመደብ መሆኑ ነው የሚታወቀው። በድርጅቱ ውስጥ ያለው የሰው ሃይል እንደየማስፈፀም አቅሙና እንደ ክሂሎቱ እየታየ የድርጅቱን ተልእኮዎች ለማስፈጸም የሚመደብ መሆኑን ነው። የሚመድበውም ድርጅት ነው፡፡ ምንም ያህል ከባድ ተልእኮዎችም ቢሆኑ እንኳን የተሰለፈበትን አላማ እስካሳካ ድረስ ተቀብሎ የመሄድ ድርጅታዊ ዲሲፕሊን በኢህአዴግ ቤት ውስጥ የዳበረና የኖረ ነው፡፡

እስከዛሬ እንደታየው፤ ሰው እንደፍላጎቱና እንደምኞቱ አይመደብም፡፡ ለድርጅቱ አላማና ተልእኮ እስከሚጠቅምና ለህዝብ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት እስከተቻለ ድረስ የትኛውም ቦታ ተመድቦ ይሰራል፡፡ ይሄ ድርጅታዊ መርህ ነው፡፡ በድርጅቱ ታሪክም ታላቁ መሪን ጨምሮ በርካታ የድርጅቱ ነባር አመራሮች ሁሌም ከአንደበታቸው የማይጠፋው ድርጅቴ እስከፈለገኝና እዚህ ቦታ ስራ እስካለኝ ድረስ የሚል አባባል ነበር፡፡

በመሆኑም፣ ብዙዎቹም በርካታ አስቸጋሪ ተልእኮዎችን ጭምር እየወሰዱ መስዋእትነት ለመክፈል

ተገደዋል፡፡ እናም በኢህአዴግ ቤት ጠቅላይ ሚኒስትር ሹመት የትርምስና የጭቅጭቅ አጀንዳ አይደለም! ሊሆንም አይችልም! አልሆነም። ለዚህም ነው የስልጣንና ወንበር አምላኪዎች ወግና ምኞት በቀላሉ ሊመክን የቻለው።

ለዶ/ር አቢይ አህመድ መልካም የስራ ዘመን እንመኛለን!!!